# ኢክሌዚያ

## ተጠርተው የወጡ ማለትነው

Hesed multimedia

COUNSELING TEAM PRESENTS



**ኢክሌዚያ አፍታ**

ልዩ ቆይታ ከፓስተር ተስፋዬ
ጋቢሶ ጋር


“ከወርቅና ከክቡር ዕንቍ ይልቅ ይወደዳል፤
ከማርና ከማር ወለላም ይጣፍጣል።”
— መዝሙር 19፥10
ቃሉ
ሲጣፍጥ
“ቃልህ ለጕሮሮዬ ጣፋጭ ነው፤ ከማርና
ከወለላ ይልቅ ለአፌ ጣፈጠኝ።”
— መዝሙር 119፥103

# Hesed multimedia

EKKLESIA

WEDAJE LIBE

DAILY VERSE

Join us on telegram

@juecsfcounseling

# ማውጫ



## አምድ


01 የአዘጋጁ መልዕክት

03 ኢክሌዚያ አፍታ

06 CHURCH FATHERS

10 ንወራ

ተረቴን ውሰዱ ዳቦውንም ብሉት

12 ምስባከ ሰባኪያን

15 ከዚህም ከዚያም

18 እንነጋገርበት

23 ጥበበ ሰማያት

25 ይመልሱ ይሸለሙ




ልዩ ቆይታ ከፓስተር ተስፋዬ ጋቢሶ ጋር



AMONG GREAT CLOUD OF WITNESS

# የአዘጋጁመልእክት

ውድ የኤክሌዢያ መጽሄት ተከታታዮች እንዴት ናችሁ? በታማኙ ጌታ በምህረቱ ባለጠጋ በሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ ፍቅር ሰላም እላችዋለው። ከዚህ በፊት በ ትንሽ ወረቀት የምናቃት ኢክሌሺያ እነሆ አሁን አድጋ ተመንድጋ በ digital መልክ ተጨማሪ አምዶችን አካታ ወደናንተ መጥታላችዋለች።
ታዲያ እኔም ሁሉንም አምድ እድታነቡ እየጋበዝኳችሁ ጥቂት ከዮሴፍ ታሪክ በመነሳት ወደ እግዚአብሄር ፍቃድ በሚወስዱን ፈተናዎች ተጠላልፈን እንዳንወድቅ እንጠንቀቅ ልላችሁ ወደድኩ።

ዮሴፍ አባቱ ያዕቆብ ከሌሎቹ ልጆቹ አስበልጦ የሚወደው 11ኛ ልጁ ነበር። አባቱም በጣም ይወደው ስለነበር ወንድሞቹ ይቀኑበት ነበር። አንድ ቀን በህልሙ የእርሱ ነዶ ቆሞ የወንድሞቹ ነዶዎች ግን ለእርሱ ሲሰግዱ አየ። በሌላም ጊዜ እንዲሁ ፀሀይ፣ ጨረቃና 11 ከዋክብት (አባቱን፣ እናቱንና ወንድሞቹን የሚወክል) ለእርሱ ሲሰግዱ አየ። እንኳን ዘንቦብሽ እንዲሉ እነኝህን ህልሞች ሲሰሙ ይበልጥ ወንድሞቹ ጠሉት። ከዛም በአንዱ ቀን ሊገድሉት ተማከሩ። እንዲሞትም ጉዳጎድ ውስጥ ጣሉት። ይሁዳ ግን አንድ ሀሳብ አቀረበ "ወንድማችንን መግደል እና አሟሟቱን መደበቅ ምን ይጠቅመናል? ከዚህ ይልቅ ለእስማኤላውያን ነጋዴዎች እንሸጠው። እጃችንን ግን በእርሱ ላይ አናንሳ። ምንም ቢሆን ወንድማችን፤ ስጋችን ነው" አለ።

በዚህም ሀሳብ መሠረት በ20 ብር ሸጡት። መቼም ዮሴፍ በገዛ ወንድሞቹ በመሸጡ ምን ያህል ልቡ እንደተሰበረ መገመት አይከብድም። እሱ ግን የእግዚአብሔር ፈቃድ በህይወቱ እየተፈጸመ በሚያልፍበት በነዚህ ፈተናዎች ተጠላልፎ አልወደቀም። ምክንያቱም በወንድሞቹ ላይ ቂም አልያዘም፣ እኔም እድሉና አጋጣሚው ይመቻችልኝ እንጂ እነሱ እንደበደሉኝ እኔም እንደዛው አደርግባቸዋለው አላለም፣ እድሉንም ሲያገኝ አላረገባቸውም ነበር። ለምን አላደረገም ካልን ራሱ ዮሴፍ "እናንተ እኔን ለመጉዳት አስባችሁ አድርጋችሁት ነበር..እግዚአብሄር ግን ለበጎ ነገር አዋለው" እንዳለው መንገዱ ለጉዳት ቢመስለም ጌታ ግን ለመልካም እንዳደረገው ስለተረዳ ነበር።

እኛም በህይወታችን የእግዚአብሄር ፈቃድ እንዲፈፀም በብዙ ውጣውረዶች መውደቅ መነሳቶች እናልፋለን። ቃሉ በሮሜ 8:28 “እግዚአብሔርንም ለሚወዱት እንደ አሳቡም ለተጠሩት ነገር ሁሉ ለበጎ እንዲደረግ እናውቃለን።” እንደሚል ለኛ ጌታን ለምንወድ እንደሃሳቡም ለተጠራን ነገር ሁሉ ለመልካም ነው። ነገር ግን ሁሌም በዚህ መንገድ ስናልፍ እኛን ወደ ፍቃዱ በማያስጠጉን ፈተናዎች እንዳንወድቅ እንጠንቀቅ።


መልስ ይመለሳል
በጸሎት
ልብ ይጠበቃል

# ኢክሌዢያ አፍታ

ሰላም ውድ የኢክሌዚያ መጽኤት አንባቢያን ዛሬ በ መጀመሪያው የ ኢክሌዚያ አፍታ አምዳችን እጅግ ከምናከብረው እና ከምንወደው ከ ፓስተር ተስፋዬ ጋቢሶ ጋር የአፍታ ቆይታ እናደርጋለን ተከታተሉን።

ኢክሌዢያ:-ሰላም ፓስተር እንኳን ደህና መጡ

ፓስተር:-እግዚአብሄር ይመስገን

ኢክሌዢያ:- ጌታን እንዴት ነበር የተቀበሉት?

ፓስትር:- ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ያወቅሁት በወንጌል አማኝ ወላጆቼ በኩል ነበር። እንደ ግል አዳኜ የተቀበልሁትም በልጅነቴ ነው። ዓመቱን አላስታውስም።

ኢክሌዢያ:-እርሶ ወጣት በነበሩበት ጊዜ እና በአሁን ዘመን ወጣት መካከል ምን ልዩነት ያያሉ?

ፓስትር :- ያ ዘመንና የአሁኑ ይለያያል። አንዱ ልዩነት የዓይነት፣ የዕድልና የተግዳሮት መጠን ነው። በእኔ ዘመን የነበረው ወጣት የሚያያቸውና የሚሰማቸው ነገሮች ውስን ነበሩ። የሚበዛው ሬዲዮ ብቻ ነበር ለማዳመጥ የሚችለው። ያንንም የማያገኝ ነበር። በከተማ የሚኖሩ አንዳንዶች ቴሌቪዥን ይመለከቱ ነበር። ከትምህርት መርጃ ውጪ፣ ጋዜጣ መፅሔትና መፅሐፍ የሚያነቡ እጅግ ውስን ነበሩ። የዛሬው ወጣት በመረጃ አቀባበልና አሰጣጥ ረገድ በብዙ ይለያል ለማለት ይቻላል። መረጃ ደግሞ በባሕርይ ላይ የሚያስከትለው በጎም ክፉም ተጽእኖ ይኖረዋል። የዚያ ዘመን ወጣት ሞራል በአመዛኙ ቤተ ክርስቲያን ከመሔድ ባሻገር በፈርሃ በእግዚአብሔር የታነፀ ነበር። ፡ ወላጅ እና ታላቅ ይከበራል። ሶሻሊዝም ሲገባ ደግሞ መከባበርና እግዚአብሔርን መፍራት ተሸረሸረ። እግዚአብሔርን እስከ መኖሩም ለመካድና ለማስካድ ተሞከረ። የእኩልነት ስሜት መከባበርን ለማስወገድ ታገለ። ከባሕርይ አኳያ፣ የዛሬ ዘመን ወጣት የዚያ ዘመን እና የአሁኑ ድምር ውጤት ይመስለኛል። መልካም ዕድሎቹም ተግዳሮቶቹም የበዙ ናቸው። በእግዚአብሔር ጸጋ፣ ልክ እንደ ትናንቱ የዛሬውንም ተግዳሮት አሸንፎ ማለፍ ግን የሚቻል ነው

ኢክሌዢያ:- በዚህ ዘመን በቤተ ክርስቲያን ወስጥ ያደጉ ወጣቶችም ጭምር በተለያዩ ሱሶች ተጠምደው ይታያሉ። ቤተክርስቲያን (ለኛ ደግሞ የተማሪዎች ፌሎሺፕ) ምን ማድረግ አለባችው ይላሉ?

ፓስትር ፥ እኔ ድሮ የማየው የሲጃራ፣ የጫትና የአልኮል መጠጥ ሱስ ነበር። አሁን ሱስ የሚያስይዙ ነገሮች ዝርዝራቸው እንደበረከተ እሰማለሁ። ወጣት በምንም ዓይነት ሱስ ተጠመደ ማለት የሕይወት አላማው ተሰናከለ፤ በአጭር ቀረ፤ ጤናው ጠባዩና በሕይወት የመቀጠል ተስፋው አደጋ ላይ ወደቀ ማለት ነው። ይህን ተግዳሮት ለመቋቋም ቤተ ሰብ፣ ቤተ ክርስቲያን መሪ አገልጋዮች እና መንግሥት መተባበር ይኖርባቸዋል። የማስተማር፣ የመምከር፣ ምቹ አካባቢን መፍጠርና መጠበቅ ያሻል። የተማሪዎች ሕብረትም በየግቢው የእረኝነት አገልግሎት ስልት ነድፈው ቢተጉ ብዙዎችን ሊያተርፉ ይችላሉ ብዬ አስባለሁ።







# ኢክሌዢያ አፍታ

ኢክሌዢያ :- ማህበራዊ ድህረገጾች አጠቃቀም ላይ ለ ወጣቱ ምን ይመክራሉ?

ፓስትር:- ሱስ ከሚያስይዙና ባህርይ ላይ ተጽእኖ ከሚያሳርፉ ነገሮች አንዱ የማሕበራዊ ሚዲያ አጠቃቀም ይመስለኛል። አጠቃቀም ላይ ብልህ መሆንና ጠንካራ ዲሲፕሊን መለማመድ ያስፈልጋል። የአጠቃቀም ጥበብ ከሌለ ማሕበራዊ ሚድያ ወጥመድ ሊሆን ይችላል ብዬ አስባለሁ። የአእምሮና የስሜት እስረኛ ያደርጋል። ጊዜን ይበላል። ውጤታማነትን ይቀንሳል። የፀሎት ፍላጎትን ያጠፋል። ከቃሉ መመገቢያ ዕድልን ይሻማል። መንፈሳዊ ሕይወትን ያከሳል። ሕሊናን እያቆሸሸ ጤናን ያጎድላል። አስተሳሰብን ያበላሻል። አዎንታዊ ዝንባሌን ያዳክማል። በመሆኑም፣ የማይጠቅሙና ጎጂ ውጤት የሚያመጡትን መዝጋት ይገባል። አእምሮና ነፍስን የሚገነባ ብቻ ተመርጦና ጊዜን በጣም መጥኖ መጠቀም ይመከራል። ጥያቄው ሰንቱ ይህንን የማድረግ አቅም አለው የሚል ነው። ጉዳዩ በምክር መተጋገዝን ይጠይቃል።

ኢክሌዢያ:- ወጣቱ መካከል ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እየወጡ ባሉ "ዝማሬዎች" ትልቅ መከፋፈል ተፈጥሯል። በተለይ ደግሞ secularism የሚባለው ሃሳብ ጥያቄዎችን እየፈጠረ ነው። ለእርሶ 1 ግጥም እና ዜማ መዝሙር ለመባል ምን መስፈርት ማሟላት አለበት?

ፓስተር :- መንፈሳዊ (የወንጌል) ዝማሬ ወንጌላዊውን አስተምሕሮ ማንፀባረቅ ይኖርበታል። ወንጌላዊው አስተምሕሮ ምንና ምን እንደሚያካትት ጠይቆ መረዳትና ጠንቅቆ ማወቅ ያስፈልጋል። ለመንፈሳዊ ዝማሬ፣ ወንጌላዊውና መጽሐፍ ቅዱሳዊው ይዘት ወሳኝ ነው። ይህን የሚያደርግ ለሕይወቱ ዕድገት ሲል መጽሐፍ ቅዱስን አዘውትሮ የሚያነብና ወንጌላዊውን አስተምሕሮ የሚያስታውስ ነው። የዝማሬውም ዜማ ስሜትን ከማነሣሣት ይልቅ ሕይወትን ወደ እግዚአብሔር የማስጠጋት ዓላማና ጥበብ ያለበት ሊሆን ይገባል።

ኢክሌዢያ :-በመጨረሻ ለወጣቱ በተለይ ደግሞ ለ university ተማሪዎች ማስተላለፍ የሚፈልጉት መልእክት ካለ።

ፓስተር :-የእኔ ምክር ተማሪ ጠንክሮ ያጥና ጎበዝ ይሁን። ለልዕቀት ይሥራ። የተማሪ ነገው በዛሬ ውጤት ይወሰናል። ነገ በሥራ መስክ ተፈላጊነት የሚኖረው በዛሬ የትምሕርት ውጤት መሆኑን ማስታወስ በጠም ያስፈልጋል። እንቅስቃሴን በፕሮግራም መምራት ይጠቅማል። ለቀለም ትምሕርት፣ለአምልኮ፣ ለሕብረት፣ ለመሳሰለው ተመጣጣኝ ሰዓት በመመደብ መሥራት በሁለንተና ለማደግ መሠረታዊ ነው። ከሚያሳንፍ፣ ወይም ጎጂ በሆነ ምክር መንፈሳዊ ሕይወትን ከሚያቀጭጭና ዕድገትን ወደ ኋላ ከሚጎትት ጓደኝነት የመራቅ ብልህነትና ጥንቃቄም መታከል ይኖርበታል (መዝ 1:1-2)። «ክፉ ባልንጀርነት መልካሙን አመል ያጠፋል»(1 ቆሮ 15፡ 33)። ጥሩ መራጭ መሆን መልካም ነው። ከሁሉ በማስቀደም በየዕለቱ ከጌታ ጋር በቅርበት ለመጓዝ፣ ቃሉን ማንበብና በጸሎት ማሰላሰልን መለማማድ፣ የመከናወን ቁልፍ ስለሆነ በዚህም መትጋት አይዘንጋ።

እግዚአብሔር ይባርካችሁ። ይጠብቃችሁ። በሕይወት መንገድም ይምራችሁ። ባርኮ ለበረከትም ያውላችሁ።







# Do you know?

- Many types of food and drink have their origins within the Catholic church including the cappuccino.


- In the original languages, the Bible's word count is about 611,000.

- Tertullian is the first person to coin the word Trinity in this treatise against praxeas.

- In1631, once English-language Bibles were finally legal, publisher Robert Barker came out with a version most notable for its omission involving the 7th Commandment: "Thou shalt commit adultery." About 1,000 copies of this Sinner's Bible (aka the Adulterous Bible or the Wicked Bible) were distributed before. Only 9 of these Bibles exist today. The wicked bible surfaced online for the first time in 2008. To this day, the book's current value rose to $100,000. Bulk copies of the wicked bible were quickly discarded and destroyed, and only several copies remain today. What a difference one little word can make!








## CHURCH FATHERS- AMONG GREAT CLOUD OF WITNESSES

The writer of the epistle to the Hebrews wrote that we Christians are surrounded by such a great cloud of witness. Standing in the first century he mentioned few Old Testament saints and it was difficult for him to mention all heroes of faith and their respective story. How much more of a difficult task would it be for us to do this in the twenty first century? We simply repeat the same question that the writer asked, what more shall I say?(Heb 11:32). But in this article I am going to pick and write to you about only one church father among great multitude of saints. I choose St. Athanasius, the Father of orthodoxy for today.

The time was just on the brink of freedom from persecution under Diocletian, tetrarch of the Roman Empire. The church began to taste this freedom under the first Christian emperor Constantine. But a few years later Arius, an Alexandrian presbyter, began to teach concerning Christ that there was a time He was not. This teaching denied the divinity of Christ. As a result, the fourth century church began to face crisis, dispute and division. For the devil works not only in persecution but also through deception (false teaching) and corruption. This dispute was so great it became a concern for Emperor Constantine, for it became a threat for the unity of the empire. Therefore, he convened the first ecumenical council, the council of Nicea. More than 250 bishops attended the council. Most of them bear the mark of Jesus on their body from torture under the former emperor Diocletian. St. Athanasius attended the council as a voteless deacon with his mentor bishop Alexander of Alexandria. At the council, Arianism was condemned as a heresy and the Nicene Creed was formulated. But the controversy continued after the council due to the Arian bishops and emperors. Three years later bishop Alexander died, and St. Athanasius was ordained as the bishop of the Alexandrian church. It became his full time duty to defend the Nicene Creed, to contend for orthodoxy.








## CHURCH FATHERS- AMONG GREAT CLOUD OF WITNESSES

Athanasius was an Egyptian by birth and a Greek by education. He was raised in a Christian family. He completed his Christian and liberal education at the famous catechetical school at Alexandria, the second most important city in the Roman Empire next to Rome. St. Athanasius had not yet reached the canonical age (30 years) when he was ordained as bishop of Alexandrian church. He was a virtuous man as witnessed by his own contemporary Gregory of Nazianzus. He once said, In praising Athanasius I shall be praising virtue because he had, or, to speak more truly, he has embraced virtue in its entirety. He continued In praising virtue I shall be praising God who gives virtue to men. He is known as one of four great eastern doctor of faith in the Catholic Church. And he is labeled as the father of orthodoxy by the Eastern Orthodox Church.

Much of his life was occupied by the struggle with Arian bishops and emperors. He was exiled five times under four emperors. He spent 17 of 45years of his service in exile from Trier (modern day Germany) to Rome, and from Rome to the Egyptian desert. He was notable for his work on the matter of the incarnation especially on his books Deincarnatione, Contra Gentes, his Festal letters- some of which have bearing on the New Testament cannons. The letters of Serapion- which defended the deity of the Holy Spirit and Four orations against the Arians- his dogmatic masterpiece, The life of saint Antony were also among his notable works. His effort gained success after his death. Arianism was defeated once and for all at the second ecumenical council, the council of Constantinople.

His life struggle teaches us one thing, as Paul wrote, For we cannot do anything against the truth, but only for the truth (2cor 13:8). We should seek the truth, hear the truth, learn the truth, love the truth and defend the truth until death. And finally, truth prevails! as Jan Hus screamed while burning at stake.







## CHURCH FATHERS- AMONG GREAT CLOUD OF WITNESSES

I shall close this article with the Nicene Creed that St. Athanasius was contending for:

We believe in one God,
The Father Almighty,
maker of heaven and earth,
of all things visible and invisible.

And in one Lord Jesus Christ,
The only-begotten Son of God,
begotten of the Father before all ages;
God of God, Light of Light,
very God of very God;
begotten, not made,
being of one substance with the Father, by whom all things were made.
Who, for us men for our salvation, came down from heaven,
and was incarnate by the Holy Spirit of the Virgin Mary, and was made man;
and was crucified also for us under Pontius Pilate; He suffered and was buried;
and the third day He rose again, according to the Scriptures;
and ascended into heaven, and sits on the right hand of the Father;
and He shall come again, with glory, to judge the quick and the dead;
whose kingdom shall have no end.

And I believe in the Holy Ghost,
The Lord and Giver of Life;
who proceeds from the Father and the Son;
who with the Father and the Son together is worshipped and glorified;
who spoke by the prophets.

And I believe one holy catholic and apostolic Church.
I acknowledge one baptism for the remission of sins;
and I look for the resurrection of the dead,
And the life of the world to come. Amen!!



# ግብዝነት የሌለበት ፍቅር



# ንወራ - ተረቴን ዉሰዱ ዳቦዉንም ብሉት

ተረት ተረት ተብሎ ተጀምሮ የላ...ም በረት(የመሰረት) በሚል የጣፈጠ የልጅ አንደበት ደሞ ተቀጥሎ፥ አዝናኝ ሆነ አስለቃሽ የአድማጩን ልብ የሚሰርቀው ተረት ተተርቶ ካበቃ ኋላ ተራቹ "ተረቴን መልሱ አፌን በዳቦ አብሱ" ብሎ ይዘጋዋል። ይህን ማለቱም ተረት ነገርኩህ አንተም አንድ ንገረኝ ለነገርኩበትም ለአፌ የምበላዉን ስጠኝ ማለቱ ነው። በሌላ አባባል "ነፃ የተባለ ነገር የለም" ነው ነገሩ።

የኛም ክርስትና ተረቴን መልስ(ሽ) እየሆነ ሳይመጣ አልቀረም። ስንቶቻችን ነን መልካም ያረግንላቸው ሰዎች እኛ ያሰብነውን በጎ ምላሽ ሳይሰጡን ልባችንን ያንገበገቡት? ስንቶቹስ ናቸው ልባችንን የሰበሩት? እኛም ደሞ "ያገናኘን" ብለን ወይ ልናረግላቸው ያሰብነውን ያስቀረን ወይ ደሞ "ተራው የኔ ነው የኔ" የሚለውን መዝሙር እየዘመርን ቀን ጠብቀን ዋጋቸውን የሰጠናቸው? ለምን? ላረግነው መልካም ሁሉ ተረታችን እንዲመለስ አፋችን ደሞ በዳቦ እንዲታበስ እየጠበቅን ስላደረግን ነው። ሲያስቀሩት ደሞ የተጎጂነት ስሜት ስለተሰማን፤ ምክንያቱም እነሱ አይወቁት እንጂ እኛ በጎ ያረግንላቸው ጊዜ በልባችን ዉል አስፈርመናቸዋል። ዉሉ ላይ ደሞ ይኸው አሁን አረኩልህ አንተ ደሞ እኔ ስፈልግ ከች ትልልኛለህ! የሚል ዉል፥ ግን ያረኩልህ እንደዉለታ ነው የሚል ፊርማ ደሞ በጥጉ ላይ ጠቀስ ተደርጓል። ታድያ ጠብቀን መምጣታችን ለዛ አይደል? እንጂማ ሰዎቹ የሚያውቁት ነፃ ዉለታ መሆኑን ነው። እኛ ጋር ግን ሌላ አጀንዳ አስቀምጠንላቸዋል።

የምንንሰፈሰፍላቸው እንዲንሰፈሰፉልን፣ ከጎናቸው የነሆነው ነገ እንዲገኙልን፣ ገንዘብ የሰጠናቸው እንዲሰጡን አስቦ ማረጉን ቃሉ አላስተማረንም።እነሱም ግዴታ የለባቸውም! እኛ ደስ ብሎን ላረግንላቸው ዳቦ ጋግረህ ጥራኝ ማለቱ ጥያቄ ያስነሳል። ክርስትና በነጻ የተሰጠን ባርያዎች ጥቂት ላረግነው ምላሽ መጠበቅ ክርስቶስ ትቶልን የሄደውን የከባድ ቀላል መንገድ ፈር እየለቀቅን መሄዳችንን ያሳያል።

አብ ከኛ ምንም ላያገኝ ልጁን በመስጠት (ዮሐ 3:16)፥ ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስ ደሞ ምክንያታዊ ያልሆነውን መስጠት ራሱ አሳይቶንና እንኖረው ዘንድ አስተምሮን ሄዷል። ይህን ያረገበትም ከሰማይም ከምድርም በነፃ እንደተቀበልን በነፃ እንሰጥ ዘንድ እንዳንሸቃቅጥ ነው (ማቴ 10:8)። እውነተኛ የሆነውን መልካምነት መኖር ለአለማዊ ሰው የሚጠቅም ነው ለኛ ግን ትዕዛዝ ነው (ሉቃ 6:27-34)። በጌታም በእኛም ዘንድ ከተለምዶ ባለፈ በመስጠት ዉስጥ ያለውን ትልቅ ደስታ ሐዋርያትም ጌታችንም ተናግረዋል (ዕብ 13:16፣ ሐዋ 20:35፣ ሉቃ 10:33-35፣ 19:8)።



በቃሉም "ያበደርከውን ተውለት" (ሉቃ 6:35፣ ዘዳ 15:2) ያለው የሰጠናቸውን አይደለም፥ ያበደርናቸውን እንኳን (ሞልቶላቸው ቢመልሱ መቀበላችን ባይቀርም) እንደሚመልሱልን እያሰብን ግን መስጠት እንደሌለብን ያስተምረናል። ምክንያቱም በሰማይ ድብን አርጎ የሚከፍለንን ጌታን ተስፋችን እንድናደርግ ስለፈለገ ነው (1ጢሞ 6:18-19፣ ሉቃ 12:33)። ካልሆነማ የነሱን ምላሽ እየጠበቅን አንድ ሁለት እያልን ቆጥረን ያረግን ከሆነ የረሱት ቀን ወይ ክፋት ሲያስታቅፉን "እፀድቅ ብዬ ባዝላት ተንጠልጥላ ቀረች" እንዲል ተረቱ ተጎጂነት ተሰምቶን ያዘልናቸውን ስናፈርጥ ካልቻልንም ቂም ይዘን አብረን ልንፈርጥ ወይ ልናቆም ነው (ማቴ 5:42፡ "ለሚለምንህ ስጥ፥ ከአንተም ይበደር ዘንድ ከሚወደው ፊቀቅ አትበል")። ስለዚህ ክርስቶሳዊ የሆነውን ክርስትና እያንጸባረቅን በማይለዋወጥ መልካምነት እንዲባርከን እና እንዲባርካቸው እንጠይቀው፤ እነርሱንም ጌታ ካልረዳ መልካም ሊወጣቸው ስለማይችል። ስራችንም በቃሉ እየተቃኘን እንድንመላለስ እርሱ ይርዳን። አሜን!

ይህችን ግጥም እንካችሁ

## መስጠት ማበደር ናት?

ተረትን አጉርሶ መልሶ እያስተፋ
አዋቂ ህጻኑ እድሜውን ሲገፋ
በተለምዶ ባህል በልክነት ምካር
መለበሚያው ላልቶ የህሊናው አውታር
መስጠት አይደል መስጠት
መስጠት ማበደር ናት
ሄዳ እንዳትቀር ግዝት አድርግባት
ወይ ታለችበት ሄደህ ምትቃርማት
መስጠት ማበደር ናት
ተብሎ ሲኖረው የኑሮ ቅንባሮ
ህዝቡ ተደናብሮ
የተጎረሰ ተረት ሳይዋጥ ሲተፋ
ከናፍርት ታብሰው ድፎ እየተደፋ
የመስጠት አንድምታ ከስሩ ሲገታ
ከንፈር እንድታብስ ወዲህ ምናስጠራት
መስጠት ተጎሳቁላ መልኳን ቀይረናት
የልጆች ተረት ተረት ሆና አገኘናት።



# ምስባከ ሰባኪያን

## አምልኮ

አምልኮን ለመግለጽ መሞከር ባህርን በወጭት ጠልቆ ለመጨረስ እንደመሞከር ነው። ቢሆንም ግን በመጽሐፍ ቅዱሳችን ላይ በግልፅ የሰፈረ ከጥንት የነበረ የእግዚአብሔር ሰዎች የህይወት መርህና መንገድ ነውና በአጭሩም ቢሆን ልናወራበት ይገባል።



አምልኮ መለኮት ለሆነ አካል የሚደረግ ሀይማኖታዊ መሰጠት ነዉ። ይህ ጠቅለል ባለ መልኩ ሊቀርብ የሚችል የአምልኮ ትርጓሜ ሲሆን እንደ ክርስቲያን ደግሞ መለኮት የሆነው አምላካችን እግዚአብሔር እንደመሆኑ አምልኮ ማለት ለእግዚአብሔር የሚደረግ መሰጠት ወይም ለእርሱ የሚቀርብ ስግደት፣ ውዳሴ፣ ምስጋና፣ አክብሮት እና መደነቅ ማለት ነው። አምልኮ የአምላክን መኖር ከማወቅ፤ ይህም አምላክ በሁሉም ላይ ገዢ እና ባለስልጣን እንደሆነ ከመረዳት፥ የእርሱንም ስራ ከማስተዋል ይጀምራል። በመጀመሪያ የእኛ መፈጠርና በአምሳሉ መስራታቸን በራሱ የእርሱን መልክ በምድር እንድናንጸባርቅ፣ በማንነታችን ክብሩን እንድናወራ እንደሆነ በመጨረሻም ሁሉ ተጠቅልሎ ለእርሱ ክብር እንደሚጠናቀቅ መረዳት ተገቢ ነው። "፤ ሁሉ ከእርሱና በእርሱ ለእርሱም ነውና፤ ለእርሱ ለዘላለም ክብር ይሁን፤ አሜን።"
(ሮሜ 11: 36) ይህ ብቻ ሳይሆን ደግሞ እግዚአብሔርን ከመታዘዝ እና ከመዉደድ የሚመነጭ ስጦታ እንደሆነ መረዳት ያስፈልጋል።



አምልኮ በእግዚአብሔር ፊት ጣፋጭ የሆነ የመዓዛ ሽታን የተወደደ መሥዋዕት አድርጎ ማቅረብ ነው። በዘፍጥረት 4: 3-4 ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ የሰው ልጅ ለእግዚአብሔር ያቀረበውን መሥዋዕት እናገኛለን። በቃየን እና በአቤል ከቀረበው መሥዋዕት ቀጥሎ ኖኅ ከዚያም አብርሃም ከዚያም ደግሞ በእግዚአብሔር የተመረጠው የአብርሃም ዘር ለእግዚአብሔር መሥዋዕትን ሲያቀርብ ኖሯል። ይህ ሁሉ ቀጥሎ ደግሞ በአዲሱ ኪዳን በክርስቶስ በተደረገልን ቤዛነት አምልኳችን ታድሷል። በሚያረጁና በሚሞቱ ካህናት ሳይሆን በዘለዓለማዊው ሊቀካህን በእየሱስ ክርስቶስ ወደ አብ በመግባታችን፤ በህግ ሳይሆን በፀጋ፣ በእየሱስ በኩል፣ በእምነት፣ በእውነትና በመንፈስ በሚደረግ አምልኮ ፊቱ እንቀርባለን።









# አምልኮ

ሌላው መረዳት ያለብን ነገር እግዚአብሔርን ስላመለክነው የምንጨምርለት ክብር ስላላመለክነው ደግሞ የምንቀንስበት ግርማ እንደሌለው ነው። በክብርና በግርማ ከዘለዓለም በፊት የነበረ፥ አሁንም ያለ፥ ደግሞ ለዘለዓለም የሚኖር አምላክ ነው። "፤ እርሱ ብቻ የማይሞት ነው፤ ማንም ሊቀርበው በማይችል ብርሃን ይኖራል፤ አንድ ሰው እንኳ አላየውም ሊያይም አይቻለውም፤ ለእርሱ ክብርና የዘላለም ኃይል ይሁን፤ አሜን።" (1ኛ ወደ ጢሞቴዎስ 6: 16)

ስለዚህ አምልኮ እግዚአብሔር የሆነውን ማንነቱን ማሳየት፣ በተገለጠልን መንገድ እና ልክ በህይወታችንና በአንደበታችን ፍሬ ማክበር ነው። ዕብራውያን 13: 15-16 "እንግዲህ ዘወትር ለእግዚአብሔር የምስጋናን መሥዋዕት፥ ማለት ለስሙ የሚመሰክሩ የከንፈሮችን ፍሬ፥ በእርሱ እናቅርብለት። ነገር ግን መልካም ማድረግን ለሌሎችም ማካፈልን አትርሱ፤ እንዲህ ያለው መሥዋዕት እግዚአብሔርን ደስ ያሰኘዋልና።" እንደሚል አምልኳችን በአንደበታችን እንዲሁም በድርጊታችን ሊገለፅ ይችላል። ከዚህ ባለፈ ግን የተደረገልንን እና የምናውቀውን ሁሉ ስለጌታችን፥ ለጌታችን መናገር መልካም ሆኖ ሳለ በተቃራኒው ደግሞ ያልኖርነውን ኑሮ በአንደበታችን አሽሞንሙነን እርሱን ልንደልለው አንችልም። "አንደበቱን ሳይገታ ልቡን እያሳተ እግዚአብሔርን የሚያመልክ የሚመስለው ማንም ቢኖር የእርሱ አምልኮ ከንቱ ነው። ንጹሕ የሆነ ነውርም የሌለበት አምልኮ በእግዚአብሔር አብ ዘንድ ይህ ነው፤ ወላጆች የሌላቸውን ልጆች ባልቴቶችንም በመከራቸው መጠየቅ፥ በዓለምም ከሚገኝ እድፍ ሰውነቱን መጠበቅ ነው። (የያዕቆብ መልእክት 1: 26-27 )

ይህን ብዬ ልጨርስ፡ አምልኮ በደመነፍስ ወይም በስሜት በቸልተኝነት የሚሰጥ ሳይሆን ለሚገባው አምላክ ግንዛቤን በተሞላ አስተውሎት እንዲሁም በሙሉ ፈቃደኝነት የሚደረግ የህይወት ልምምድ ነው። ለዚህ የጠራን ጌታ ይመስገን።

"ምስጋናና ውበት በፊቱ፥ ቅዱስነትና ግርማ በመቅደሱ ውስጥ ናቸው። የአሕዛብ ወገኖች፥ ለእግዚአብሔር አምጡ፥ ክብርና ምስጋናን ለእግዚአብሔር አምጡ፤ ለስሙ የሚገባ ክብርን ለእግዚአብሔር አምጡ፤ ቍርባን ያዙ ወደ አደባባዮችም ግቡ። በቅድስናው ስፍራ ለእግዚአብሔር ስገዱ፤ ምድር ሁሉ በፊቱ ትነዋወጥ።" (መዝሙረ ዳዊት 96: 6-9)




# የዜማ ቅምሻ

ሃይማኖቴን እምነቴን አንተን ጌታ
ከላይ አንዴ ያገኘሁ የኔን ቤዛ
ያምላኬን ጸጋ በመሴሰን አለውጥም
ንጉሴን አንተን ኢየሱሴን አልክደም

ሃይማኖቴን ማተሜን አንተን ጌታ
ከላይ አንዴ ያገኘሁ የኔን ቤዛ
ያምላኬን ጸጋ በመሴሰን አለውጥም
ንጉሴን አንተን ኢየሱስን አልክድም

አልደራደርም ባንተ ጉዳይ
አንደ ቀልድ አላይም የሆንከውን መስቀል ላይ
ከአብ ዘንድ ያገኘሁ ወዱ ስጦታ አንተ ነህ እና የኔ
ቤዛ

በመረቀልን በአዲሱ እና በህያው መንገድ
ወደ ቅድስቲቱ በኢየሱስ ቀርበን
የእውነትን እውቀት ካገኘን ወይ
ወደን በሃጢአት እንዴት እንጸናለን
ወደን ሃጢአትን እንዴት እናደርጋለን

ዘማሪት ሰላም ደስታ

# ከዚህም ከዛም-

# እንጡራ ወንጌል

## (ከንጉሴ ቡልቻ "ወቅታዊ ዘላለማዊ" መፅሃፍ ተቀንጭቦ የተወሰደ)

" በብዙ አይነትና በብዙ ጎዳና " የሚናገረው ጌታ አንድ ዋና ባህርይ ቁርጥ ያለ መልዕክት ማቅረቡ ነው። የመናገር በሽታ የለበትም፣ የራሱንም ድምፅ የማሰማት ጉጉት አይቀሰቅሰውም፤ ለጌጥ ለጨዋታም አይሰለፍም። መልዕክቱን ያውቀዋል፤ ግቡም የሰው ልጅ ደህንነት ነው። እግዚአብሄር በቃል ይሁን በሌላ ወደ ሰው የሚሰደውን መልዕክት ባወጣ ያውጣው አይወረውረውም። "የምልካት ቃሌ የምሻውን ታደርጋለች እንጂ በከንቱ ወደ እኔ አትመለስም" ማለቱ ማነጣጠሩን፣ የማይስትም መሆኑን ያመላክታል።

እኛ ስንናገር ወይ ስንፅፍ፣ በተለይ የወንጌል መልዕክት ለማስተላለፍ ስንሞክር የምንናገረውን አጥርተን እናውቃለን ወይስ "ግብሩን እንደማያውቅ ተዋናይ መድረኩ ላይ አጓጉል እንወራጫለን?" ወንጌሉን የማያውቅ ማነው? ደግሞ እርሱ ለመናገር ምን ያስቸግርና ነው ለውይይት የሚነሳ የተባለ እንደሆነ፣ የምንለው ያልገባቸው ወይም ያደናገራቸው ሰዎች መልስ ይስጡበት እላለው።

ወንጌሉ ምን አይደለም ??

፦የስነ ምግባር ሃተታ አይደለም

"ከክፋት ደግነት ሳይሻል አይቀርም" የሚለው ዘይቤ "ለጤናማ ለማህበራዊ ኑሮም መቸም ይጠቅምሃል፣ ኪስህ እንዳይራቆት፣ ራስህን እንዳትታመም ሰው እንዳይጠላህ ይቺን ኪኒን ዋጣት" የሚል አስማታዊ ምክር አይደለም። የክርስቶስ ወንጌል ሰዎችን ከእኩያን አስተሳሰቦች አላቆ ገባርያነ ሰናይ (መልካም አድራጊዎች) እንዲሆኑ ማስቻሉ እርግጥ ነው። ሆኖም ብዙ እምነቶች ተመሳሳይ ሞራላዊ ምክር ለጋሾች ናቸውና የወንጌል ልዩነቱ (uniqueness) ምንድን ነው? ቀዳሚ ማንነቱ ከዚህ ይጠልቃል። ደግሞም በጎ ምግባር የወንጌል ስራ ውጤት እንጂ ወንጌሉ ራሱ አይደለም።

፦የድንቃድንቆች ርችት ብቻ አይደለም



# አንጡራ ወንጌል


## (ከንጉሴ ቡልቻ "ወቅታዊ ዘላለማዊ" መፅሃፍ ተቀንጭቦ የተወሰደ)

ሰውዬው ወደ ፀሎት ቤት ሄዶ ልጁ ከቡዳ መንፈስ ብትላቀቅለት፣ ንግዱ አይቶ የማያውቀውን ትርፍ ቢያስገኝለት፣ ወይም በተንኮል ሲሸምቅበት የነበረው ጎረቤቱ ጠላቱ እግር ስር ወድቆ ቢለማመጠው፣ የሆነለት ነገር ሁሉ መልካም ሆኖ ሳለ ብቻውን የወንጌል ቃል አይደለም። በጠቅላላው የወንጌል መልዕክት ውስጥ ተገቢውን ስፍራ መያዝ አለበት። "ወይ ጉድ …… ወይ ጉድ ……የጌታ ታምር" ብቻ ከማለት አልፎ ሙሉ የሆነ ወንጌል እንዲያቀርብ ይጠበቃል።

:-የቡድን ወይም የድርጅት ማስተዋወቂያ ጥሪም አይደለም የወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያን (ከነስማቸው ወንጌላውያን) የወንጌሉን ቃል ሲዘሩ ሩጫቸው " እዚህ ቦታ፣ እዚህ ፀሎት ቤት፣ እዚህ ስብሰባ ላይ ብትገኙ፣ ይህን ቀመር ብትሰሩ በርግጥ ትድናላቹ አይበሉ። በእኛ ቋንቋ ብቻ ለሚናገሩና አብረውን ለሚውሉ ብቻ የተገለጠ አድርገን ወንጌሉን የክለባችን መተዳደሪያ ደንብ አናድርገው። የክርስቶስ ወንጌል አርቴፊሻል አጥሮችን እንደሌሉ ነው የሚቆጥራቸው። እኛም አንጡራውን ወንጌል እንፈልገው። እንግዲያው የወንጌል ቡጡ (ዋናው) ምንድን ነው?

ወንጌል:- ክርስቶስ ማዕከሉ ነው፤ መስቀል ስብከቱ ነው፤ እምነት ጥሪው ነው።




የመዳን
ቀን
ዛሬ ነው

# እንነጋገርበት

## በሕግ አምላክ!

ውድ አንባቢያን! እንዴት ናችሁ? ለዛሬ በዚህ አምድ ስለ ሕግ (Moral Law) እንድንነጋገር ይህን ጽሁፍ ይዤ ብቅ ብያለሁ። በዚህ ጽሁፍ የአዲስ ኪዳን አማኝ ሕጉን በተመለከተ ሊኖረው ስለተገባው መፅሐፍ ቅዱሳዊ አቋም ለመዳሰስ እንሞክራለን። ወጋችን ፍሬ እንዲኖረው ታዲያ የተሣሣቱ ቅድመ-ግንዛቤዎቻችንን (preconceptions) ወደ ጎን መተው ይገባናል። በትሕትና ከቃሉ ስለ ሕጉ እናወራለን፤ እንነጋገራለን። በዚህ ጽሁፍ ሕግ ተብሎ የተገለጸው አስርቱን ትዕዛዛት ብቻ እንደሚወክል ልብ ይሏል። ጥቂት የማይባሉ አማኞች ሕጉ ላይ ያላቸው ጭፍን ጥላቻ (prejudice) እጅጉን አሣሣቢ ነው። ከነዚሁም አንዳንዶቹ "ሕጉን የመፈፀም ግዴታ የለብንም" ወይንም "ሕጉ ተሽሯል" የሚል አቋም ሲያንፀባርቁ ይታያል። መጽሐፍ እንደሚል ደግሞ ሕጉን መጣስ ኃጢአት ነው (1ዮሐ 3:4)። ስለሆነም ይህ አስተምህሮ ለርኩሰት ነፃነትን የሚሰጥ ሆኖ እናገኘዋለን። የእነርሱ አቋም አመክንዮአዊና መፅሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆነ በግማሽ እውነት ላይ የተመሰረተ አስተምህሮ ነው። ይሄ ደግሞ የተለመደ የአጋንንት አሰራር ነው። ሰይጣን የብርሃን መልአክ እንዲመስል ራሱን ይለውጣልና። ይህ አስተምህሮ ከጥንቷ ቤተክርስቲያን ጀምሮ እንደነበር መጽሐፍ ይነግረናል (ገላ 5:13፣ ሮሜ 6:1)። አስተምህሮው በተሐድሶና በድህረ-ተሐድሶ ቤተክርስቲያን ብዙ ውዝግቦችን አስነስቷል። በ17ኛው ክፍለዘመን በማሳቹሴትስ አስተምህሮው ያስነሳው ውዝግብ ለምሳሌ ያህል የሚጠቀስ ነው። ከዚህ ውዝግብ መቶ አመታት ቀደም ብሎ የማርቲን ሉተር ጓደኛና የመፅሐፍ ቅዱስ አስተማሪ የነበረው ጆሃንስ አግሪኮላ በተሐድሶው ዘመን የዚህ አስተምህሮ ፋና ወጊ ተደርጎ ይቆጠራል። ማርቲን ሉተር የእርሱን አስተምህሮ በመቃወም "Against The Antinomian " የተሰኘውን ጽሁፉን በ1540 ዓ.ም ለማሣተም በቅቷል፤ ለእርሱና ለተከታዮቹ አዲስ ስያሜ በማውጣት ጭምር (Antinomian)። በፅሁፌ ለስማቸው የአማርኛ አቻ ትርጉም ስላጣሁለት "ሕግ ለምኔ" የሚል ስያሜን ለመጠቀም ተገድጃለሁ። ለመሆኑ መጽሐፍ ቅዱሳችን ስለ እነርሱ አስተምህሮ ምን ምላሽ ይሰጠናል? ሕግ ለምኔዎች እንደሚሉት በርግጥ ሕጉን መፈጸም አይገባንምን? እስቲ ከጽሁፉ ጋር አብረን እንዝለቅ!







# በሕግ አምላክ!

ይብዛም ይነስም ስለ ሕግ ባለን እውቀት ሕግ የአስገዳጅነት ባህርይ እንዳለው እናውቃለን። ደግሞም ሕግ አውጪ አካል እንዳለና፣ አጨቃጫቂ ሁኔታዎች ሲፈጠሩም ሕግ ተርጓሚ አካል እንዳለ ግልጽ ነው። ደግሞም በዕለተዕለት ኑሯችን ለምንሰራባቸው፣ ለምንማርባቸው ተቋማት እንዲሁም አገራችን ለምታወጣቸው ሕጎች እንገዛለን። ሕግ በኑሯችንም ብቻ ሳይሆን በክርስትናችንም ትልቅ ስፍራ አለው። መጽሐፍ ቅዱሳችንን ራሱ የተመለከትን እንደሆነ የመጀመሪያዎቹ አምስት መጽሐፍት የሕግ መጽሐፍት በመባል ይታወቃሉ። ሕጉን ከቃሉ ቃሉን ከሕጉ ነጥሎ ማየት አይቻልም። ሕጉን ደግሞ የሰጠን እግዚአብሔር ነው። ለዚህም ነው የጌታ ወንድም ያዕቆብ በመልዕክቱ ላይ ሕጉን “የንጉስ ህግ” (Royal Law) ብሎ የጻፈልን (ያዕ 2፡8)። ሕጉ የምድር ዳርቻ ፈጣሪ፣ የዘላለም አምላክ የነገሥታት ንጉሥ የጌቶችም ጌታ ከሆነው ከእግዚአብሔር ዘንድ የተሰጠ ትዕዛዝ ነው። "ሕጉ ቅዱስ ነው ትእዛዚቱም ቅድስትና ጻድቅት በጎም ናት" (ሮሜ 7፡12)። ሕጉ ፍጹም፣ ንጹህና ቅን የሆነ፣ ከእግዚአብሔር ዙፋን ችሎት የወጣና የእርሱንም ቅድስና የሚያንጸባርቅ ነው። ታዲያ ለዚህ ታላቅ ንጉሥ ምንኛ ልንታዘዝ ይገባን ይሆን? እርሱን አለመታዘዝ እንዲህ ብሎ ከተጻፈው ከነብዩው ቃል ጋር አይጋጭምን? “ልጅ አባቱን፣ ባሪያም ጌታውን ያከብራል፤ እኔ አባት ከሆንኩ፣ መከበሬ የት አለ ጌታስ ከሆንሁ መፈራቴ የት አለ?” (ሚል 1፡6) እግዚአብሔር አባታችንም ጌታችንም ስለሆነ ልንታዘዘው ይገባናል። በመቀጠልም እርሱ የሰጠን ሕግጋት በመጀመሪያይቱ ትዕዛዝ ማለትም እርሱን ፍጹም በሆነ መሠጠት በመውደድ ደግሞም በሁለተኛይቱ ትዕዛዝ ጎረቤትን እንደራስ አድርገን በመውደድ ይደመደማል (ማቴ 22፡37-40)። የሕጉ ግብ ፍቅር ነው። ክፉውን ከደጉ የምንለይበት መመዘኛ ነው። እግዚአብሔር ሕግ ሰጪ ብቻ ሳይሆን ሕግ ተርጓሚውም እርሱ ራሱ ነው። ማለትም የሕጉ ትክክለኛ ትርጉም የሚገኘው እርሱ ጋር ነው። ይህንንም ለማረጋገጥ የኢየሱስ ክርስቶስ አገልግሎት መመልከት ብቻ በቂ ነው። በእርሱ ጊዜ የነበሩ ፈሪሳውያን አንዳንድ ጊዜ ጥብቅና የቆሙለትን ሕጉን እንደሚጠበቅባቸው በትክክል ሲያስተምሩ አይገኙም። አንዳንዴ ሕጉ የሚጠይቀውን ተፈፃሚነት ሙሉ በሙሉ አያስተምሩም (ማቴ 5፡28)። ለዚህም ነው ብዙ ጊዜ ወንጌላትን ስናነብ “እንደዚህ እንደተባለ ሰምታችኋል፤ እኔ ግን እላችኋለሁ” የሚል ቃል ከክርስቶስ አንደበት የማይጠፋው (ማቴ 5፡21)። እንዲህም እያለ በስልጣን ቃል ሕጉን ያስተምር ነበር። በዚህም ምክንያት ሕዝቡ በእርሱ እጅግ ይደነቅ ነበር። ፈሪሳውያን አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ሕጉን በሕዝቡ ላይ ቀንበር ያደርጉበታል (ሉቃ 6፡ 2)። ስለዚህም ነው ኢየሱስም በአንድ ወቅት ፈሪሳውያን በከሰሱት ጊዜ የሰው ልጅ የሰንበት ጌታ እንደሆነ የነገራቸው። ይህንንም ያላቸው እርሱ የሕጉ ሰጪ ብቻ ሳይሆን ተርጓሚውም እርሱ ራሱ በመሆኑ ነበር። እግዚአብሔር አስቀድሞ በነብያቱ የመንፈስ ቅዱስን የተስፋ ቃል ሰጥቶን ነበር። ይህም የተስፋ ቃል ኢየሱስ ክርስቶስ በደሙ በሆነው በአዲሱ ኪዳን ተፈጽሟል። የተሰጠንም መንፈስ ቅዱስ ሕጉን በልባችን እንዳኖረ በልቡናችንም እንደጻፈ መጽሐፍ ይነግረናል(ዕብ 10፡16)። ይህ ለአማኞች የተሰጠ ገጸበረከት ነው። ይህ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነታ እግዚአብሔር ለሕጉ በአዲስ ኪዳን የሰጠውን አጽንዖት ያሳያል። የህይወት መንፈስ ሕግ የተባለው እርሱ ሕጉን የምንፈጽምበት አቅም ዕለት ዕለት ይሰጠናል (ሮሜ 8፡2)። ሕጉን የሰጠን አምላክ እርሱን የምንታዘዝበትን አቅም በቅዱሱ መንፈስ አማካይነት ይሰጠናል። ሕጉ መንፈሳዊ ነው (ሮሜ7፡14)። ምንጩ ሰማያዊ፣ አላማውም ሰማያዊ ነው።

# በሕግ አምላክ!

መቀጠልም ወደ ሕግ ለምኔዎች ልመልሳችሁና ሳሙኤል ቦልተን የተባለ አንድ ሰው ላስተዋውቃችሁ። ይህ ሰው በ17ኛው ክፍለዘመን በኢንግሊዝ አገር ይኖር የነበረ የነገረመለኮት ሊቅ ነበር። እንደ አውሮፓውያኑ ዘመን አቆጣጠር በ1645 ዓ.ም ባሳተመው "The True Bounds Of Christian Freedom" በተሰኘው መጽሐፉ የሕጉን መሻርንና እርሱን ከመታዘዝ ነጻ ስለ መሆን የሚተርከውን የሕግ ለምኔዎች አስተምህሮ ለማስተባበል ይረዳሉ ያላቸውን ሁለት ነጥቦችን አስቀምጦልናል። የመጀመሪያው ነጥብ ሕጉ አማኞች አሁንም ቢሆን ሊመላለሱበት የሚገባ መንገድ ስለመሆኑ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ሕግና ጸጋ የሚስማሙ እንጂ የማይጋጩ ስለመሆናቸው ነው። እነዚህን ሁለት ነጥቦች ካረጋገጥን ይለናል ሳሙኤል ቦልተን በመጽሐፉ የሕግ ለምኔዎችን አስተምህሮ ፉርሽ ማድረግ ይቻላል(ገጽ 35)። ሳሙኤል ቦልተን እንደጻፈልን የመጀመሪያው ነጥብ አሁንም ቢሆን እኛ የአዲስ ኪዳን አማኞች ሕጉን ልንታዘዝ ይገባናል። ለዚህም ነው ሐዋርያው ጳውሎስ በሮሜ መልዕክቱ በአሕዛብ ሁሉ መካከል ከእምነት የሚነሳ መታዘዝ እንዲገኝ ጸጋንና ሐዋርያነትን ተቀብለናል ብሎ የጻፈልን(ሮሜ 1:5)። ጥሪያችን በእምነት ብቻ፣ በጸጋ ብቻ፣ በክርስቶስ ኢየሱስ በኩል ለመልካም ስራ ነው(ቲቶ 3:8)። እርሱን ለመታዘዝ፣ መልካሙን ስራ ሁሉ ለማድረግ የቀናን እንድንሆን ስለእኛ ክርስቶስ ራሱን ሰጥቷል(ቲቶ 2:14) ። ጆን ኦውን ይህንን ሃሳብ "On The Christian Life" በተሰኘው መጽሐፉ ዳግም በተወለደው አማኝ ልብ ሕጉን ባተመው በመንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔርን የምንታዘዝበት አዲስ መርሕ ተቀብለናል ብሎ የጻፈልን(ገጽ 53)። ሕግን በመፈጸም አንጸድቅም። ይህንን ለማድረግ መሞከር በባርነት ቀንበር ውስጥ መውደቅ ነው። ከዚህ ባርነት በክርስቶስ በማመን ነጻ ወጥተናል። የጨዋይቱ ልጆች ነን እንጂ የባሪያይቱ አይደለንም። ይህ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነታ ግን ሕጉ ተሽሯል ወይንም ሕጉን የመፈጸም ግዴታ የለብንም የሚል ድምዳሜ ላይ እንድንደርስ አያደርገንም። ጄ.አይ. ፓከር እንደጻፈው ክርስቲያንና ሕጉ የሚኖራቸው ግንኙነት የሚገለጸው ከመጽድቅ(Justification)አንጻር ሳይሆን በወንጌል በማመን ካገኘነው ልጅነት(adoption) አንጻር እንጂ። ልጅ ደግሞ አባቱን ይሰማዋል፤ ይታዘዘዋል። በተጨማሪም ደግሞ የምንታዘዘው ለጌታችን ካለን ፍቅር የተነሳ ነው። ለዚህም ነው ክርስቶስ ብትወዱኝስ ትዕዛዜን ጠብቁ ያለን(ዮሐ 14:15)። ዳግም እንደተወለደ አማኝ በእግዚአብሔር ሕግ ሐሴት እናደርጋለን(ሮሜ 7:22)። ስለዚህም ዳዊት በመዝሙሩ እንዲህ ብሏል፦ "አቤቱ፤ ሕግህን ምንኛ ወደድሁ!" (መዝ 119:97)። አማኝ ሕጉን ያሰላስል፤ ሕጉን ይጠብቃል፤ ይህን ማድረግ የዘወትር ተግባሩ ነው(መዝ 119:55)።







# በሕግ አምላክ!



ሌላኛው ፉርሽ ማድረግ ያለብን ሁለተኛው ነጥብ በብዙ ክርስቲያኖች ዘንድ የሚንጸባረቅ ሃሳብ ነው። ይህም ሕግና ጸጋን ምንም የማይስማሙና ቅብብሎሽ የሌላቸው አድርገዉ ማሰባቸው ነው። ይህ አስተሳሰብ ምናልባትም ሕግና ጸጋ ያላቸውን የባህርይ ልዩነት ከመገንዘብ የመነጨ ሊሆን ይችላል። ሕግ እንደ ጸጋ በእምነት ላይ የተመሰረተ አይደለም(ገላ 3:12)። ሕግ ስራን ይጠይቃል፤ ጸጋ ግን ነጻ ስጦታ ነው። ሕግና ጸጋ ያላቸው መሰረታዊ ልዩነት ግን ቅብብሎሽ የሌላቸው(Incompatible) አድርገን እንድናስባቸው ማድረግ የለበትም። ሕግ የተሰጠው ከመተላለፋችን የተነሳ ነው(ገላ 3:19)። ሕጉ ስጋዊነታችንን ይገልጠዋል(ሮሜ 7:14)። ሕጉ መላው የሰው ዘር ሁሉ ሀጢአተኛና የእግዚአብሔር ቁጣ የተገባው እንደሆነ በግልጽ ያስረዳል። ይህንንም ሐዋርያው ጳውሎስ በሮሜ መልዕክቱ እንዲህ ጽፎልናል፦ "እንግዲህ አፍ ሁሉ እንዲዘጋና ዓለም በሙሉ ለእግዚአብሔር መልስ እንዲሰጥ ሕግ የሚናገረው ሁሉ ከሕግ በታች ላሉት እንደሆነ፣ እናውቃለንና" (ሮሜ 3:19)። ከዚህም የተነሳ እንደ ሐዋርያው ጴጥሮስ "እኛም አባቶቻችንም አቃተን" ብለን እንድን ዘንድ ወደ ክርስቶስ ኢየሱስ ጸጋ እንድንሸሽ ያደርገናል(ሐዋ 15:10-11)። ሕጉ በእግዚአብሔር ፊት እራሳችንን አዋርደን ለድነታችን የኢየሱስን መስቀል እንድንመለከት ያደርገናል። በዚህም ምክንያት እግዚአብሔር ሕጉ ክርስቶስ እስኪመጣ ድረስ ሞግዚት አድርጎ ሰጥቶናል(ገላ 3:14)። የሕጉ መሰጠት የጸጋውን የተስፋ ቃል አይሽርም(ገላ 3:17)። ይልቁንም ስለ ክርስቶስ ይመሰክራል እንጂ። ፊልጶስ ለናትናኤል እንዳለው ሙሴ በሕግ ነብያቱም የጻፉልን ስለ ዮሴፍ ልጅ ስለ ናዝሬቱ ኢየሱስ ይመሰክራሉ(ዮሐ 1:45)። ደግሞም እግዚአብሔር በኪዳን ያጸናውን የተስፋ ቃል ከ430 አመት በኃላ በተሰጠው ሕግ ፈጽሞ አይሽርም(ገላ 3:17)። በሌላም በኩል ስንመለከት ጸጋው ሕጉን አይሽርም። በጸጋው እንዲያው የዳነው ሕጉ የሚጠይቀውን ጽድቅ ሙሉ በሙሉ ስለ እኛ በፈጸመው በክርስቶስ ኢየሱስ በማመን እንደሆነ ልብ ይሏል። አምነን ወደ ጸጋው ከመጣን በኋላም እንኳን ሕጉ ድካማችንን እንደመስታወት በግልጽ ያሳየናል። ስለዚህም ራሳችንን አዋርደን ወደ ጸጋው ዙፋን እንድንቀርብ ያደርገናል። ቅዱስ ኦገስጢን እንደተናገረው ሕጉ ያዘናል፤ ጸጋ ደግሞ የምንታዘዝበት አቅም ይሰጠናል። ጸጋው ደግሞ ለቅድስናና ክርስቶስን ወደ መምሰል እንድናድግ ወደ ሕጉ መልሶ ይመራናል። ሳሙኤል ቦልተን ጸጋው ላዳነን ክርስቲያኖች "ሕጉ ወደ ጸጋው የመራችሁ እናንተ አሁን ደግሞ ወንጌሉ ወደ ሕጉ መልሶ ይምራችሁ!" ብሎ ይመክረናል። ሕግ ጸጋን፣ ጸጋ ደግሞ ሕጉን ፈጽሞ አልሻረም። እውነቱ እኛ ሐጢአተኛ መሆናችን ነው። ይህንን የሚያስረዳው እግዚአብሔር ለሙሴ በሲና ተራራ የሰጠው ሕጉ ነው። አሁን ግን አርነት የሚያወጣንን እውነትንና የምንድንበት ጸጋ በሙላት በኢየሱስ ተቀብለናል(ዮሐ 1:45)።





# በሕግ አምላክ!



በስተመጨረሻም የሕግ ለምኔዎችን አስተምህሮ በአገሬ ሰው ብሂል የመዘነው እንደሆነም ውሃ የሚያነሳ ሆኖ አናገኘውም። ይህንንም ለማሣየት ያህል የተማረከብን “በህግ አምላክ!” በሚል ርዕስ አቶ ጌታቸው በለጠ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ሰኔ 8 /2011 እትም ላይ ወዳስነበቡት ጹሁፍ ልውሰዳችሁ። በጽሁፋቸውም በአሁኑ ጊዜ በአገራችን "በሕግ አምላክ! የሚለው ጠንካራ እሴት እየደበዘዘ ስለመሆኑን አስፍረዋል። ቀጥለውም “በቀዳሚዎቹ ዘመናት“በሕግ አምላክ!” የሚለው የፍትሕ መማጠኛ ኃይለ ቃል መሠረቱ እጅግ የጠበቀና የተጎናጸፈው የእሴት ፀጋም የምንኮራበት ማኅበረሰባዊ ሀብታችን (Social Capital) እንደነበር አይዘነጋም። አገሬው ስለ ሕግ ሃያልነት ሲናገር "በሕግ አምላክ ሲባል እንኳን ሰው ወራጅ ውሃ ይቆማል" ይል ነበር። ሕግ ተፈጥሮንም እስከማቆም ሃይል እንዳለው አድርጎ ለመግለፅ ምን ዓይነት በሕግ የፀና እምነት ቢኖር ነበር ያስብላል። ነበር እያኮራም እንዳያሰኝ ሰጋሁ እንጂ!" ብለው አስነብበውናል አቶ ጌታቸው በለጠ በጽሁፋቸው። በተመሳሳይ መልኩ ደግሞ የእግዚአብሔርን ሕግ ማክበር ከክርስቲያን ማህበረሰብ የሚጠበቅና የሚያኮራ እሴት(virtue) ነው። በነጻ ያዳነውን አምላኩን መታዘዙ የክርስቲያን ወጉ ነው። ይህ ክርስቲያናዊ እሴት ግን ከሕግ ለምኔዎች(Antinomians) ተማርኮባቸዋል። በጸጋ አስታከው ከኃጢአን መንደር ተገኝተዋል። ከሕግ ባርነት ወጥተናል ብለው የኃጢአት ባርነት ውስጥ ገብተዋል። በደሙ ተዋጅተናል ብለው ለፈሰሰላቸው ደም እንኳን የሚመጥን ኑሮ የላቸውም። ጸጋን በአፋቸው ይጠሩታል እንጂ ፈጽሞ አያውቁትም። በመጨረሻም ሳሙኤል ቦልተን ያስቀመጠልንን ሁለቱን ነጥቦች በመጽሐፍ ቅዱስ አስረድተን የሕግ ለምኔዎች አስተምህሮ ፉርሽ ማድረግ ችለናል። አስተምህሯቸውም ሕጉን ከሰጠን ከእግዚአብሔር፣ ከአዲስ ኪዳን፣ ከሐዋርያት አስተምህሮ፣ ከክርስቲያንናዊ ሕይወት፣ ከቤተክርስቲያን አባቶች አስተምህሮ ይብሱንም ደግሞ ለአንተ ቆመንልሀል ከሚሉለት "ከጸጋ አስተምህሮ" ጋር የሚጋጭ ሆኖ አግኝተነዋል። አስተምህሮው አመክንዮአዊና መጽሀፍ ቅዱሳዊ አይደለም። ለዚህም ነው በዚህ አምድ ሕግ ለምኔዎችን "በሕግ አምላክ!" እላቸው ዘንድ የወደድኩት። በጸጋ በእምነት ድነናል። የተገረዘውን በእምነት፣ ያልተገረዘውንም በዚያው እምነት የሚያጸድቅ አንድ እግዚአብሔር ብቻ ነውና። ታዲያ እንዲህ ከሆነ ከእምነት የተነሣ ሕግን ዋጋ የሌለው እናደርግ ይሆን? ፈጽሞ አይደረግም፤ ሕጉን እናጸናለን እንጂ" (ሮሜ 3:30-31)።





# ጥበበ ሰማያት



## እኔ እና መማሬ

ምህረትህ እና እኔ ምን እና ምንድን ነን?
መቼ ተጀምሬ መቼ ላበቃ ነው
ባንተነትህ ሞገስ እንዲህ የተቃኘሁ?
የመክሰሜን ስምጠት፣
የአጠፋፌን ጥልቀት
ጠልቄ አውቀዋለሁ ፣
ኖሬ አይቼዋለሁ
መማሬን ብቻ ነው እንዲነው እማልለው
ለምህረትህ ብቻ አቻ ስምን አጣሁ!

ከፅድቅህ ማዕከል ከመውደድህ ማዕበል
ለሚተኛ አለም ለሚያሸልብ ምድር
እንቅልፍ ሆኜ ነበር  የምከርም የምኖር ።
ብሆንም!
ስትምር የገረመኝ...
ስፍራው ሰማያዊ ...
ባህሪው መንፈሳዊ ...
በሆነ በረከት ሞልተህ ስትባርከኝ!

ስትምር የገረመኝ...
ከእኔ እውር ስራ፣
ከእኔ ጉስቁል አቋም
ምንም ሳትጨምር ምንም ሳታጣምር!

ይህ ሁሉ እንዲህ ነው ሚያስብለኝ
እኔ እና መማሬ
ምህረትህ እና እኔ ምን እና ምንድን ነን?
እኔ እኮ
ከፍጥረቴ ሁላ ቁጣ ነው የሚያውቀኝ
ከጉዞዬ ሁላ ማጣት ነው የኖረኝ።
ብሆንም!
ስትምር የገረመኝ...
ሁሉንም ትተህ ነው በምህረትህ ሀጫ አዲስ ያደረግከኝ።
እንዲ ሆንኩ  እንዲያ ሆንኩ... ማለቱ ይቅርብኝ
ምህረትህ እራሱ አንተን አከለብኝ!

# Do you know?

- Christianity is the most persecuted religion in the world. Estimated 70 million Christians are killed for their faith.


- The Dead Sea Scrolls are the oldest set of Biblical manuscripts we have in existence. In 1947, these ancient documents were discovered in 12 caves in the West Bank. A Bedouin shepherd found the initial scrolls while looking for a lost goat. He threw a rock into the cave and heard the sound of shattered pots. Inside the cave, were the first seven scrolls, containing the entire manuscript of the Book of Isaiah and other ancient non-biblical literature.

- There are 21 recorded dreams(not visions) and most of them were seen by two different men named Joseph!(11 to be exact).

- Over 100 million copies of the Bible are sold each year.

# ይመልሱ ይሸለሙ

## የነብያት ስም



### ወደ ታች

**1** ከታላላቅ ነብያት መካከል እንደ ዋነኛ ይቆጠራል

**2** የብኤሪ ልጅ

**5** በደረቅ አጥንቶች የተሞላ ሸለቆን በራዕይ ያየ

**7** ንጉስ ናቡከደነጾር ያለመዉን ሕልም እግዚአቢሄር የገለጠለት ነብይ

**9** የስሙ ትርጉም “መልዕክተኛዬ” ማለት ነው

**10** ኢዮአቄም ሊቀ ካህን በነበረበት ዘመን ከካህናት ወገን ለነበሩት አለቃ በመሆን አያቱን የተካ

**11** እግዚአቢሄር “በዚህ ስፍራ ሚስት አታግባ ወንዶችና ሴቶች አይኑሩህ”ሲል ያዘዘው

**13** ስለ ነነዌ ውድቀት የጻፈ ሰው

**15** የስሙ ትርጉም “የእግዚአቢሄር አገልጋይ” ማለት ነው

## የነብያት ስም

### ወደ ጎን

**3** በሀዋሪያት ስራ መጽሃፍ ውስጥ ብቻ ስሙ የተጠቀሰ ነብይ

**4** እስራኤልን የሚመለከት የትንቢት ቃል ያላካተቱ መለዕክቶች የነበሩት

**6** ትንቢቱን የትውልድን ሀረጉን በመዘርዘር የሚጀምር

**8** ሞሬት ከምትባል ከተማ የወጣ ሰው

**12** በዓሳ ሆድ ውስጥ ሆኖ ወደ እግዚአቢሄር የጸለየ

**14** ከበዓላት ቀን በአንዱ በመወለዱ የስሙ ትርጓሜ “በዓል” የሆነ

**15** ይህ ነብይ በግ በማርባትና የባሉጥ ፍሬ በመልቀም የሚኖር ነበር

ቀድሞ ለመለሰ
የሞባይል ካርድ ሽልማት

Contact us ...
telegram @eyuyegeta


Dombo
Nafoli
Abeni
Nati
Mercy
Nazri
አምደኞች
Editor
Josh
Join us
Telegram... t.me/juecsfcounseling
Facebook... juecsfcounselling official
phone number.. 0913632217Or0919407455


Hesed multimedia
የድምጽ መልዕክት
Coming soon
Counseling team presents
ወዳጄ ልቤ